# የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የሚካሄድ ወሲብ ወይም ጋብቻ /INCEST/

**ከአማረ መስፍን**

## 1. ትርጉም

- ማናቸውንም ዓይነት የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የሚፈፀም ጋብቻ ወይንም ግብረ ሥጋ
- አንድ ሰው ከጎሣው ውጭ የሚፈፅመው ጋብቻ Exogamy
- አንድ ሰው በጎሣው ውስጥ የሚፈፅመው ጋብቻ Endogamy

## 2. አጀማመሩ

### 2.1 በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

- የሙሴ ሕግ ከመሰጠቱ አስቀድሞ በተለይም የሰው ልጆች ቁጥር አነስተኛ በነበረበት ወቅት በዝምድና መሃል የሚደረግ ጋብቻ የሚፈቀድ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነበር
  - **የአዳም ልጆች ዘፍ 5÷1 - 5፤ 4÷16 - 18**
  - **የኖህ ቤተሰቦች ዘፍ 8÷15 - 19፤ 9÷1 - 7**
- ቀጣይም በሆኑ ዓመታት እስከ ሙሴ ሕግ መሰጠት ድረስ የኖሩ ሰዎች ሲጠቀሙበት ኖረዋል
  - ሣራ ለአብርሃም የአባቱ ልጅ (ግማሽ እህቱ) ነበረች ዘፍ 20÷12
  - የሙሴ፣ የአሮንና የማርያም ወላጆች በአጎትና በአክስት ደረጃ ባለ የዝምድና እርከን የተጋቡ ነበሩ ዘጸ 6÷20፤ ዘኁ 26÷59

### 2.2 በባዕዳን አማልክት ታሪክ

- በእስራኤል አጎራባቾች ዘንድ በሚመለኩ ባዕዳን አማልክት አፈ ታሪክ አማልክቱ በእህትና በወንድም ደረጃ ሳይቀር ጋብቻን የፈፀሙ እንደነበሩ ይነገራል ለአብነት ያህል፡-
  - ዚዮስና ሄራ ወንድምና እህት እንደዚሁም ባልና ሚስት ነበሩ
  - ወላጆቻቸው ክሮነስና ሪያም እንደዚሁ
  - የባቢሎን አማልክት ከነበሩት ኒምሮድ የሴሚራሚስ ልጅ ሲሆን ቀጥሎም ባልዋ ሆኗል
  - ከግብፅ አማልክት ኦሲሪስ የኔፍቲስ ጉዲፈቻ ልጅ ሲሆን በኋላ ባልዋ ሆኗል

## 3. በዘመናችን ያለው ገጽታ

በዝምድና መሃል የሚደረግ ጋብቻ ወይንም ግብረ ሥጋ ከባህል ወደ ባህል የተለያየ ገጽታ አለው:: ይኸውም በየባህሉ ደንብና ሥርዓት መሠረት የዝምድናውን መለኪያ የሚያጠብቁና የሚያላሉ መስፈርቶች ሰላሉ ዝምድናው በሚላላበት ጎን ጋብቻን መፈፀም ይፈቀዳል ለምሳሌ:-

- Tobriad Islanders

  (በፓፑዋ ኒው ጊኒ ውስጥ በምትገኝ ቶብራያድ በተባለችውና 12 ሺህ ያህል ነዋሪዎች ባሉዋት ደሴት ላይ የሚኖሩ ነዋሪዎች ናቸው)

  - የዘር ሃረጋቸው በእናት ወገን ነው የሚቆጠረው ስለዚህ በማናቸውም የእናት ወገን በኩል በሚኖር ዝምድና መሃል ጋብቻ የተከለከለ ሲሆን በአባት ወገን ግን ይቻላል
- በአብዛኛው የዓረቡ ዓለም ክፍሎች ውስጥ 50 % የሚሆኑት ጋብቻዎች ከአጎትና ከአክስት ልጅ ጀምሮ ባሉ የዝምድና እርከኖች መሃል የሚፈፀሙ ናቸው
- በሕንድ ውስጥ ግን በደቡባዊው ክፍል በዝምድና መሃል ጋብቻ የሚፈቀድ ሲሆን በሰሜናዊው ክፍል ግን አይፈቀድም
- በዝምድና መሃል የሚፈፀሙ ጋብቻዎችንም አስመልክቶ በሕግ የሚተላለፉ ቅጣቶችም እንደዚሁ ከቦታ ወደ ቦታ ይለያያሉ
  - በሮም አገዛዝ ወቅት በዝምድና መሃል የሚፈፀም ጋብቻ በ295 ዓ.ም. በመንግሥት አዋጅ ተከልክሏል
  - በኒውዮርክ ሕግ መሠረት ይህን ዓይነት ጋብቻ ወይንም ግብረ ሥጋ እስከ 4 ድረስ ለሚሆኑ ዓመታት በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን
  - በአውስትራሊያ ደግሞ እስከ 25 ዓመታት ድረስ በጽኑ እስራት ሊያስቀጣ ይችላል

## 4. መጽሐፍ ቅዱስ በዝምድና መሃል ስለሚፈጸም ጋብቻና ግብረ ሥጋ ምን ይላል ?

### 4.1 ብሉይ ኪዳን

- አስቀድሞ እንደተጠቀሰው በዝምድና መሃል የሚፈፀም ጋብቻ ከሙሴ ሕግ መሰጠት አስቀድሞ የግዴታም ነበር:: ሆኖም ግን በሕጉ መሰጠት በኋላ ከተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ ይህ ልምምድ ተከልክሏል::

**1ሀ** በሕጉ ጋብቻን የሚከለክል የዝምድና ርዝመት ዘሌ 18÷9 - 14፤ 20÷17, 19

**1ለ** ጠቅለል ያለ መግለጫ ዘሌ 18÷6

"ማንም ሰው ግብረ ሥጋ ለመፈፀም ወደ ማንኛውም የሥጋ ዘመዱ አይቅረብ::"

**2ለ** የዝምድና መጠን ሦስት ደረጃዎች (በወንዱ በኩል)

*1ሐ የመጀመሪያ ደረጃ ቅርበት*

⇒ *እናት፣ የእንጀራ እናት፣ እህት (ሙሉ ወይንም ግማሽ)፣ የልጅ ልጅ*

*2ሐ ሁለተኛ ደረጃ ቅርበት*

⇒ *አክስት*

*3ሐ ሦስተኛ ደረጃ ቅርበት*

⇒ *የወንድም ሚስት፣ ምራት (የልጅ ሚስት)፣ የሚስት እህት፣ የሚስት ልጅ፣ የአጎት ሚስት*

**2ሀ *ጋብቻው የተከለከለባቸው ምክንያቶች* (ዘሌ 18፥1 - 5፤ 24 - 30፤ 20፥22 - 26**

1ለ እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑ እስራኤል የእርሱን ቅድስና ማንፀባረቅ ስላለባት

2ለ በኖሩበት በግብፅ ምድር ያሉት አሕዛብ ያደርጉ የነበረውን ርኩሰት እነርሱም እንዳይደግሙ

3ለ እግዚአብሔር በሰጣቸው ምድር በከነዓን አምላካቸው እንዲባርካቸው የከነዓናውያንን ብልሹና አስጸያፊ አኗኗር እንዳይለማመዱ

## 4.2 በአዲስ ኪዳን

### 1ሀ *መግቢያ*

- *ትዳርና ግብረ ሥጋን አስመልክቶ የአዲስ ኪዳን ዘመን እኛ ካለንበት ዘመን ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ የሆኑ ልምምዶች የሚታዩበት ዘመን ነበር ለምሳሌ፡-*
  - *ጋብቻና ፍቺ የተለመዱ ነበሩ*
  - የቤተሰብ ምጣኔ ተለምዶ ነበር (ሮማውያን ከሁለት በላይ ልጆችን አይወልዱም ነበር)
  - *የተለያዩ ልቅ ግብረ ሥጋዊ ልምምዶች ይታዩ ነበር*

### 2ሀ *ግብረ ሥጋዊ ልምምዶች በአዲስ ኪዳን*

- *የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ቤተ ክርስቲያን ግብረ ሥጋን አስመልክቶ ከገጠሟት ተግዳሮቶች ዋነኛው ግብረ ሥጋዊ ጋጠወጥነት (ኢ-ሞራላዊነት)* [Sexual immorality] *ነበር*
- *ይህም በግሪክኛው* "Porneia" *በሚል ስም የተገለጠው ሲሆን ጳውሎስ በየመልእክቶቹ ሊያነሣው የሞከረው ጉዳይ ነው፤ ለምሳሌ፡-* **ሮሜ 1፥18 - 27፤ 1ቆሮ 5፥1,9 - 11፤6፥9,13, 15 - 16,18፤ 7፥2,10 - 18፤ 2ቆሮ 12፥21፤ ገላ 5፥19፤ ኤፌ 5፥3,5፤ ቆላ 3፥5፤ 1ተሰ 4፥3 1ጢሞ 1፥10፤ ዕብ 13፥4**
- *ኢየሱስ በማር* **7፥21 - 23** *ላይ ሰውን የሚያረክስ ልምምድ እንደሆነ ጠቅሷል*

- የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የአይሁድና የአሕዛብን ግንኙነት ፈጽሞ የማይሞከር ከሚያደርጉት ልምምዶች ዋነኛው አድርገው ይወስዱት ነበር ሐዋ 15÷20,29
- የዕብራውያን ጸሐፊ በእግዚአብሔር ከሚያስፈርዱ ኃጢአቶች አንዱ ነው ይለዋል ዕብ 13÷4
- ይሁዳም እንደዚሁ ይህን ያደረጉ ከእግዚአብሔር ፍርድ እንዳላመለጡ ጽፏል ይሁዳ 7

## 3ሀ የግብረ ሥጋዊ ጋጠወጥነት (ኢ-ሞራላዊነት) ትርጉም / Sexual immorality /

- ግሪክኛው "Porneia" እና ከቃሉ የሚረቡት (porneuo, porne, pornos, ekporneuo) ሰፋ ያለ ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም የግብረ ሥጋዊ ኃጢአትን ትርጓሜ የሚያካልሉ ቃላት ናቸው ማቴ 15÷19፤ ማር 7÷21 1ቆሮ 7÷2
- "Porn" የሚለው ቃል በጥሬው ሴተኛ አዳሪነት ወይንም ግልሙትና ማለት ነው

## 4ሀ አዲስ ኪዳናችን ለግብረ ሥጋዊ ኃጢአቶች የሚሰጠው መጠነ ሰፊ የትርጉም ክልል

- አዲስ ኪዳናችን ግብረ ሥጋዊ ርኵሰትን ለመግለጽ የተጠቀመባቸው ቃላት ሰፋ ያለ ትርጓሜን ያዘሉ ቃላት ናቸው:: ስለዚህ ከዘመድ ጋር የሚፈጸም ግብረ ሥጋን አስመልክቶ በተናጠል ሕግ አልተደነገገም፤ ሆኖም ይህ ኃጢአት ግብረ ሥጋዊ ርኵሰት ከተባሉት እንደ አንዱ ተፈርጇል::
- ለምሳሌ አመንዝራነት (ማቴ 5÷27) የሚያካትታቸው ግብረ ሥጋዊ ኃጢአቶች :-
  - ያለ ምክንያት ሚስትን መፍታት፣ ወይንም የተፈታችውን ማግባት ማቴ 5÷32፤ ዕብ 13÷4፤ 1ቆሮ 6÷9
  - ሴሰኝነት (Promiscuity) / ዝሙት ዮሐ 8÷41፤ 1ቆሮ 7÷2፤ 1ጢሞ 1÷10፤ ዕብ 12÷16
  - ግልሙትና (harlotry) ማቴ 21÷31 - 32፤ ሉቃ 15÷30፤ 1ቆሮ 6÷15 - 18
  - ከጣዖት አምልኮ ጋር የተያያዘ ሴሰኝነት (Cultic prostitution Gk. eidoloatrai) 1ቆሮ 6÷9 ራእ 2÷14,20
  - ግብረ ሰዶማዊነት Gk. Malakoi arsenokoitai ሮሜ 1÷26 - 27 1ቆሮ 6÷9፤1ጢሞ 1÷10
  - በዝምድና መሃል የሚፈጸም ግብረ ሥጋ (Incest) 1ቆሮ 5÷1

❋ *አዲስ ኪዳን ከቃሉ ተቃራኒ የሆነን ማናቸውንም ዓይነት ግብረ ሥጋዊ ልምምድ በጥቅሉ ነው የሚያወግዘው፤ ስለዚህ በዝምድና መካከል ለሚደረግ ግብረ ሥጋ የተለየ ሕግ የለውም:: 1ተሰ 4÷2 - 8*

## 5ሀ አዲስ ኪዳን በግብረ ሥጋዊ ኃጢአቶችን አስመልክቶ ያለው መርሖች

1ለ ከማናቸውም ዓይነት ከጋብቻ ውጭ የሚፈፀሙ ግብረ ሥጋዊ ኃጢአቶች መታቀብ አማራጭ ሳይሆን ለተቀደሰ አኗኗር አንዱ መስፈርት ነው

- 1ተሰ 4÷3 ላይ ያለው "መራቅ" የሚለው ቃል (Gk. Apechesthai = keep oneself + from) መቆጠብን ሳይሆን ፈፅሞ መታቀብን የሚያመለክት ቃል ነው

2ለ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አባል ለሆኑ ሁሉ የሴሰኝነትን ሕይወት መኖር ፈጽሞ የማይሆን ነው 1ቆሮ 6÷9 - 10፤ ኤፌ 5÷5

3ለ ዝሙት በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ዋዛ የሚታይ ኀጢአት አይደለም፤ ይህን የሚለማመዱ ሁሉ ከቁጣው አያመልጡም

- ገላ 5÷19 - 21 ላይ እንደ ሥጋ ሥራ ከተጠቀሱት ኀጢአቶች ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ የተጠቀሰ ነው
- ቆላ 3÷6 ላይም እንደዚሁ

4ለ ግብረ ሥጋዊ ጋጠወጥነት ፈፃሚውን አማኝ ብቻ ሳይሆን አካሉን ሳይቀር የሚያረክስ ኃጢአት ስለሆነ ከአካሉ እስከመገለል ሊያደርስ ይችላል

- 1ቆሮ 5÷9 - 11 በዚህ ጥቅስ ከምናየው:-
  - የአማኙ ብቻ እንደ ኃጢአተኛ መቆጠርና መገለል ሴቷ (የአባቱ ሚስት) አማኝ እንዳልሆነች ያስገነዝበናል
  - ጳውሎስ ለዚህ ኃጢአት "Porneia" የሚለውን የግሪክኛ ቃል መጠቀሙ ደግሞ የልጁ አባት ወይ መፋታቱን ያለበለዚያም መሞቱን ይጠቁመናል፤ ምክንያቱም በትዳር ላይ እያሉ ኃጢአቱ ቢፈፀም ኖሮ Gk. "moicheia" (adultery) የሚለውን ቃል ይጠቀም ነበር።
  - የዚህ ዓይነቱ ዝሙት በአሕዛብ እንኳ ያለመኖሩን ጳውሎስ መጥቀሱ በሮም ሕግ ውስጥ እንኳ በዝምድና መሃል ጋብቻ መፈፀም ይከለከል እንደነበር የሚጠቁም ነው

5ለ ግብረ ሥጋዊ ኃጢአት ከሌሎች ኃጢአቶች የሚለየው "በሥጋ ላይ" የሚፈጸም ስለሆነ (1ቆሮ 6÷18) የክርስቶስን ብልቶች የሚያረክስ በመሆኑ ከባድ ኃጢአት ነው 1ቆሮ 6÷15 - 20

6ለ ሥጋችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ ነው (ጳውሎስ እዚህ ጋ የተጠቀመበት ቃል የውስጡን መቅደስ የሚወክለውን Gk. "naos" የሚለውን ቃል ነው (የውጭውን የሚወክለው ቃል Gk. "heiron" የሚለው ነው)

- ☞ *ሥጋችን* የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ስለሆነ በተለያዩ ግብረ *ሥጋ*ዊ ኃጢአቶች ልናረክሰው አይገባም

**7ለ በዋጋ ስለተገዛን የፈለግነውን በ*ሥጋ*ችን ልንደርግ አንችልም 1ቆሮ 6፥20**

- ☞ ግብረ *ሥጋ*ዊ ጋጠወጥነት የመብት ጥያቄ አይደለም፣ እያንዳንዱ ሰው ስለ ግብረ *ሥጋ*ዊ ፍላጎቱ ሚስት ሊኖረው ተፈቅዶለታል 1ቆሮ 7፥2
- ☞ ከዚህ ውጭ ግን ማንም በዋጋ የተገዛ አማኝ በዋጋ በተገዛ *ሥጋ*ው ላይ መብት የለውም